የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAG.F-06.4/4/22
ቀን 10/06/2012

ለደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

<u>ደብረማርቆስ</u>

ጉዳዩ፡ የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲን የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትን ይመለከታል

በርዕሱ የተጠቀሰው ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 28 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች፣9 ገጽ አባሪና 1 ገጽ የአተገባበር መርሃ ግብር ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

መሰረት ዳምጤ
የኦዲት ዘርፍ ም/ዋና ኦዲተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ዩኒቨርሲቲው ከዮም የኢኮኖሚ ልማት ተቋም ጋር በጋራ ለመስራት በገባው ውል ላይ በተገለፀው መሰረት እንዲሁም በአጠቃላይ በህግ አግባብ ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

    - የትምህርት ፕሮግራሞቹን ለማስተማር የተሰጠው የእውቅና ፈቃድ፤ የተመረጠበት መስፈርት እና ምክንያት፤ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ፤ ያልቀረበ መሆኑ

- ከግል ተቋሙ ጋር በአጋርነት ለመሥራት የተፈቀደበት ማስረጃ ሳይኖር በጋራ ለመሥራት ከተቋሙ ጋር ውል ስምምነት መፈፀሙ፤
- የገቢ ድርሻ ክፍፍል በቦርድም ሆነ በሚመለከተው አካል ስለመፈቀዱና የክፍፍል ስርአቱ ለዩኒቨርስቲው አዋጪ ስለመሆኑ የተደረገ የጥናት ማስረጃ፤ ያልቀረበ መሆኑ
- ትምህርቱ ሲጀመር የተመዘገቡት ተማሪዎች ብዛትና ዝርዝር፤ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ
- የድህረ ምረቃ ፕሮግራሙ በአጋርነት ከተጀመረበት ከ 2006-2008 በጀት ዓመት በተያዘው ውል መሰረት ከትርፍ ክፍፍል አቀማመጥ ላይ ለዩኒቨርሲቲው 30% ለኢንስቲትዩቱ ደግሞ 70% ስለመግባቱ ለማረጋገጥ የሚያስችል የትርፍና የኪሳራ ሂሳብ መግለጫ በተሟላ ሁኔታ ያልቀረበ በመሆኑ፤
- ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ እስከ አሁንም ድረስ ከተገኘው ገቢ ላይ በጋራ አካውንቱ ጠቅላላ የገባው የገንዘብ መጠን እና በታደሰው ውል መሰረት ለዩኒቨርሲቲው 15% ለኢንስቲትዩቱ ደግሞ 85% በትክክል ዩኒቨርስቲው ማግኘት የሚገባውን የትርፍ ክፍፍል ድርሻ ማግኘቱን ስለመደረጉ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሰነዶችን ትክክለኛ የሂሳብ ሪፖርቶች በተሟላ ሁኔታ ሊቀርቡ ያልቻሉ በመሆኑ፤

ለዩኒቨርሲቲው ገቢ የተደረገው የገንዘብ መጠን በትክክል መድረስ የሚገባው የገንዘብ መጠን መሆኑን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

2. በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ውሳኔ የተለያዩ ክፍያዎችን ለአስተባባሪ እና ለትምህርት ዝግጅት፤ ፈተና ለመፈተን፤ አሳይመንት ለማረም ብር 10.00፤ ፈተና ማረም ብር 45.00፤ የሚድዋይፈሪና ላቦራቶሪ ት/ት ኤክስቴንሽን ተማሪዎች 3ኛ ወሰነ ት/ት የተግባር ልምምድ ላሰሩ መምህራንና በተለያየ ኃላፊነት ላሉ ግለሰቦች በማናጅመንት ኮሚቴ ውሳኔ መሠረት የተከፈሉ የተለያዩ ክፍያዎች ብር 3,868,100.00 በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሳይፀድቅ የተከፈለ መሆኑ፤

3. በመንግሥት ከተፈቀደው በትምህርት ዝግጅትና ማዕረግ በክሬዲት ሀወር ብር 120.00 መሆን ሲገባው ብር 500.00 በክሬዲት ሀወር በመከፈሉ ምክንያት መከፈል ከሚገባው ብር 40,320.00 በላይ ብር 168,000.00 በመከፈሉ በልዩነት ብር 127,680.00 በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ተከፍሎ መገኘቱ፤

4. ዩኒቨርሲቲው ከአብዮት ዘለቀ ፈርኒቸር ጥገና ጋር የተለያዩ ተደራራቢ አልጋና ወንበር ጥገና ስራን ለመስራት ቢዋዋልም በውሉ ጊዜ ገደብ መሰረት ባለማስረከቡ አብዮት ዘለቀ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ድርጅት ከከተከፈለው ብር 778,548.05 መክፈል የነበረበት ቅጣት /የጉዳት ካሳ/ ብር 33,722.94 ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤

5. በህገ መንግስቱ ክልሎች በፌዴራሉ መንግሥት ንብረት ላይ ግብር ወይም ቀረጥ የማስከፈል ሥልጣን እንደማይኖራቸው የተደነገገ ቢሆንም ዩኒቨርስቲው ለደብረ ማርቆስ ከተማና ለቡሬ ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት ለዓመታዊ የቦታ ኪራይ፤ የአገልግሎት ክፍያና የሊዝ ዋጋ በድምሩ ብር 4,977,082.50 ክፍያ መፈጸሙ፤

6. ለ 12 የግንባታ ሥራ ተቋራጮች በዩኒቨርሲቲው የግንባታ ጽ/ቤት በተዘጋጀ 32 የክፍያ የምስክር ወረቀት መሠረት ብር 64,210,544.50 መከፈሉ፤

7. ዩኒቨርሲቲው ከ 5 የህንፃ ሥራ ተቋራጮች ጋር የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ሕንፃዎች ግንባታ ለማሰራት ተዋውሎ ሕንፃ ሥራው የተቋረጠ ሲሆን በዋናው ውል ብር 677,874,642.06 የተዋዋለ ሲሆን ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ብር 202,154,938.12 የተከፈላቸው ሲሆን በቅድመ ክፍያ በተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 40,848,960.06 ያልተሰበሰበ እና ያልተወራረደ መሆኑን የሥራ ተቋራጮቹ የግንባታ ሥራቸውን በማቋረጣቸው በውሉ መሠረት የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

8. ዩኒቨርሲቲውን የማገልገል ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ለሕግ ክፍል የተመራ ቢሆንም ክስ ያልተመሠረተባቸው እና ለውለታው ግዴታቸው ዋስትና የተያዘው ገንዘብ ገቢ ያልተደረገ ብር 6,047,600.00 መኖሩ፤

9. **የተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ**

ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት ብር 146,237,876.18፤ ከ 5 ዓመት እስከ 10 ዓመት

ብር 3,267,450.29፤ ጠቅላላ ድምር ብር 149,505,326.47 የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 148,559,492.30 ለአይሲቲ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ለመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አካውንት ቁጥር (1000003784995) ገቢ በማድረግ ኤልሲ ከተከፈተ በኃላ በ4 ወር ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ የተገለፀ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ሂሳቡ ያልተወራረደና የኔትወርክ ትስስሩ ሥራ ያልተከናወነ መሆኑ፤

- ❖ ከላይ ከተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 16,434,281.58 ተቀጽላ ሌጀር የሌለው ሲሆን ብር 17,064,094.63 ደግሞ የዘመን ትንታኔ /AGING ANALYSIS ያልተዘጋጀለት መሆኑ፤
- ❖ በየሂሳብ ሪፖርት ቅጾች ላይ የሠፈረው ወደ ሂሳብ ማመዘኛ ላይ ተላልፎ የዴቢትና የክሬዲት ድምር ትክለኛነት ለማረጋገጥ በዝርዝር ሲታይ ከውስጥ ገቢ በ4203 የሂሳብ መደብ ብር 555,094.03 በዴቢት የሂሳብ ሚዛን መታየት ሲገባው በዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርቱ ላይ በክሬዲት የሂሳብ ሚዛን የሚታይ መሆኑ፤

10.የተከፋይ ሂሣብ በተመለከተ፤

- በሂሳብ መደብ 5052 የፍ/ቤት መያዣ ተከፋይ ሂሳብ ብር 4,396.05 ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ድረስ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ሂሳብ ውስጥ ብር 14,294,293.85 የዘመን ትንታኔ ያልተዘጋጀለት መሆኑ፤
- በየሂሳብ ሪፖርት ቅጾች ላይ የሠፈረው ወደ ሂሳብ ማመዘኛ ላይ ተላልፎ የዴቢትና የክሬዲት ድምር ትክለኛነት ለማረጋገጥ በዝርዝር ሲታይ በተከፋይ ሂሳብ ብር 1,276,866.11 በክሬዲት የሂሳብ ሚዛን መታየት ሲገባው በዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርቱ ላይ በዴቢት የሂሳብ ሚዛን የሚታይ መሆኑ፤

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤

- ለቡሬ ካምፓስ ነባር ሕንጻዎች ጥገና ለማሠራት በቁጥር በግጨ 68/2011 በቀን መጋቢት 17/2011 ዓ.ም ታትሞ በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣው ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ ካቀረቡት ተወዳዳሪዎች መካከል አሸናፊ የሆኑት ወንድሜነህ አላምረው ጠ/ሥ/ተቋራጭ አሸናፊነታቸው በቁጥር ግዥ-3479/አሸ/01/10 በቀን 12/09/2011 ዓ.ም በተገፈላቸው ደብዳቤ መሰረት ቀርበው ውል ባለመግባታቸው ዩኒቨርሲቲውን ለኪሣራ እንደዳረገ በመግለፅ የደብረ ማርቆስ ከ//አስ/ቴክኒክ እና ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት የብር 50,000.00 በገባው ዋስትና መሠረት በኢትጵያ ንግድ ባንክ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000017960745 ገቢ እንዲያደርግ ቢጠየቅም ገቢ አለማድረጉን፤ እንዲሁም በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፤

በቡሬ ካምፓስ

- ለመማሪያ አገልግሎት ይውል የነበረ ሕንፃ B-17 ባለመታደሱ ለ1 ዓመት ያህል የቆመ መሆኑ፡፤
- በግቢው የሚገኘው ቤተመጻሕፍት ዕድሳት የሚያስፈልገው ቢሆንም በአሁኑ ወቅት አገልግሎት እየሰጠ መሆኑ፤
- ተማሪዎች መማሪያ እና መኖሪያ አገልግሎት እንዲውሉ ታስበው የተገነቡ ግንባታዎች ተጠናቀው ርክክብ ቢፈፀምም ከፍተኛ ገንዘብ የወጣባቸው ግንባታዎች አገልግሎት አለመስጠታቸው፤

በጤና ሳይንስ ኮሌጅ

- 4 የመማሪያ ክፍሎች
- 6 የመኖሪያ ክፍሎች ርክክብ ያልተፈፀመባቸው መሆኑ፤
- በመስከረም 2011 ዓ.ም ርክክብ ለመፈፀም ታስቦ ሕንፃው ላይ በታየ የመስታወት መሰነጣጠቅ ለካፌ አገልግሎት የታሰበውን ታምራት ከተባለው ሥራ ተቋራጭ ርክክብ ያለመፈፀሙና ጉዳዩ እስካሁን እልባት ያለማግኘቱ፤

ሌሎች ጉዳዮች፤

የንብረትን አያያዝን በተመለከተ፤

የዩኒቨርስቲው የንብረት አያያዝ፤ አጠቃቀም እና አስተዳደር በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ፣ በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በዋናው ግቢና በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

  ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በዕርዳታ የተሰጡ ንብረቶች

  - CBR MARSHALTEST QUANTITY -2 ከ 2 ዓመት በላይ
  - OVEN MACHINE QUANTITY -5- ከ 2 ዓመት በላይ
  - AUTOMATIC MARSHAL QUANTITY -1 ከ 2 ዓመት በላይ
  - COMPRESSIVE MACHINE QUANTITY -1 ከ 2 ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ

- -የተለያዩ ማሽኖች በእርዳታ ከመንገዶች ባለስልጣን የመጡ ከተረከቧቸው፣ሲቪያል ማሽን ፣ማርሻል ስታቲስቲከር ኦቭን ለአፈር ለሽክላ ማድረቂያ ማሽን 5 የተበላሸ፣ ድራይንገ ማሽን ፣ ኮምፓርሰር ያለአገልግሎት የተቀመጡ፡
- የተለያዩ የፊዚክስ ኢንስትሮመንት በመጀመሪያ አካባቢ በትምህርት ሚኒስቴር አማካኝነት ገቢ የተደረጉ 2000 አካባቢ የሚሆን ብሪድ ሰርኪዩት፤ አናሎግ ስሎስኮፕ ጥቅም ላይ ውሎ አሁን ግን የማይሰራ፤ ቮልት ሜትር የሚሰራና የማይሰራ ተብሎ ሳይለይ በአንድ ስቶር ተከማችቶ የሚገኝ መሆኑ፤

ቡሬ ካምፓስ

ክሊኒክ በተመለከተ

- ከዋናው ስቶር መድሀኒት ወጪ ሆኖ ወደ ዲስፔንሰር (ማከፋፈያ) ክፍል ሲመጣ ምዝገባው የሚደረገው ማንዋሊ መሆኑን እና ሪፖርቲንግ ሲስተሙ ምን ያህል መድሀኒት ተጠቀመ ምን ያህል ቀረ የሚለውን እና ምን ያህል መድሀኒት ኤክስፓየረድ /ጊዜው ያለፈበት /የሚያሳይ መረጃ

የሌለ መመድሀኒት ማስቀመጫ እና ለክሊኒኩ አገልግሎት የሚውል በቂ መደርደሪያ የሌለ መሆኑን

- ➢ ክሊኒክ ውስጥ መድሀኒቶች በባህሪያቸው ቅዝቃዜ የሚፈልጉ ከዛ ውጪ የሚበላሹ መሀኒቶች የሚቀመጡበት ማቀዝቀዣ ፍሪጅ የሌለ መሆኑን
- ➢ ጊዜ ያለፈባቸው መድሀኒቶች ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ሳይወገድ የተቀመጠ መሆኑን በኦዲት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ተሽከርካሪን በተመለከተ

- የድሮ የግብርና ንብረት የሆኑ ቁጥራቸው በርከት ያሉ የተበላሹ የተለያዩ ትራክተሮች ፣ዶዘሮች፣ ኮምባይነር፣ አሮጌ መኪና እና ሞተሮች በግቢ ውስጥና በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ኢንስቶል ተደርገው የተቀመጡ አገልግሎት የማይሰጡ ማሽኖች ሳይወገዱ ተበታትነው እንደሚገኙ ፡
- ሚስት ቡሽ መኪና ኮድ4-12317 የነዳጅ ጌጅ መቁጠሪያ የማይሰራ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

የቤተ -መጻሕፍት /የላይብረሪ/ አገልግሎትን በተመለከተ

ለተማሪዎች አገልግሎት የሚውል ላይብረሪ ቁጥር 1እና2 ውስጥ Thinclient & ethernet የተባሉት በትምህርት ሚኒስቴር የተዘረጋ መሰረተ ልማት ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰበት ቢሆንም በአሁን ሰዓት ግን አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፤

እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2009 እና በ2010 በጀት ዓመት ግኝቶችን በተመለከተ

- ❖ በዋናው ግቢ ለግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ፤ ም/ስራ አስኪያጅ እና በጽ/ቤቱ ስር ለሚገኙ ባለሙያዎች የቶፕ አፕ ክፍያ በየወሩ ብር 4000.00 እንዲከፈል የዩኒቨርስቲው ስራ አመራር በቀን 22/06/2008 በቁጥር ፕ/5966/08/08 በወሰነው መሰረት ለአምስት ባለሙያዎች ከሀምሌ/2008 እስከ ሰኔ 30/2009 በድምሩ ብር 233,599.96 አለአግባብ ተከፍሎ ተገኘ መሆኑ፣
- ❖ በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ኮሌጆች በአስተዳደር ቦታዎች (የሥራ መደቦች) ላይ የአካዳሚክ ባለሙያዎችን በተደራቢነት በመመደብ በስራ አመራር ውሳኔ

መሠረት የአንዋላይዜሽን እና የኃላፊነት አበል በድምሩ ብር 973,595.00 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

❖ ከዩኒቨርሲቲው ቦርድ ፈቃድና ዕዉቅና ውጪ ከአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት በቀን 07/12/2007 ዓ.ም. በቁጥር አካ/ጉ/ም/ፕ/348/14/07 ተዘጋጅቶ በጸደቀው የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም የአሰራር መመሪያ ቁጥር-02 መሰረት የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ላስተባበሩ ኃላፊዎች በሚል በድምሩ ብር **1,506,208.00** ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ

❖ በዋና ግቢ በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 892744 ለዶ/ር ሰይፉ አድማስ ለሃይድሮሊክና ውሃ ሃብት ትምህርት ክፍል ለ2ኛ ዲግሪ በተጋባዥነት ላስተማሩበትበረ/ፕሮፌሰር ማዕረግ ብር 120.00 መከፈል ሲገባው በሰዓት ብር 500 በመክፈሉ በብልጫ ብር **27,360.00** ከደንብና መመሪያ ውጭ **ከመደበኛ በጀት**የተከፈለ መሆኑ፤

❖ የተማሪዎች ክሉኒክ ባለሙያዎች የተረኝነት አበል ሲከፈላቸው በድምሩ ብር 114,101.86 የስራ ግብር ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፤

❖ በዩኒቨርስቲው በተለያዩ ኮሌጆች ውስጥ በ2010 በጀት አመት የተከታታይ ትምህርት መርሃ ግብር ፕሮግራም ላስተማሩ እንግዳ /ገስት/ መምህራን ለተከፈለ ክፍያ በአዋጅ አንቀጽ መሰረት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ስራ ፍቃድ ሲያቀርብ ብቻ ከክፍያው ላይ 2% ቅድመ ግብር ተቀናሽ መደረግ ሲገባ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ብቻ እንዳቀረቡ እየታወቀ 2% ብቻ በመቀነሱ በዋና ግቢ ብር 86,296.00፣በህክምና ትምህርት ቤት ብር 736,569.04 እና በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 204,208.50 በድምሩ በልዩነት ብር **1,027,073.54**ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ያልተቀነስ ግብር መገኘቱ፤

❖ በሂሳብ መደብ 4202 (የጥሬ ገንዘብ ጉድለት) ከይደነቁ ይታየው ብር 3,461.85 ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ የተመዘገበና ሳይወራረድ መገኘቱን፣

ፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት